Calgary Livery Transport Services

## መፅሔት #004

### የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማ
### የቋሚ ፖሊሲ ኮሚቴ ሪፖርት እና የባለድርሻ-አካል የመልስ ሪፖርት፥ የሰማነው ነገር

ማርች 1, 2021

---

ይህ መፅሔት በማርች 5, 2021 ስለሚለጠፈው መጪው የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማ ህትመት ለኢንዱስትሪ ባለ-ድርሻ አካላት ለማሳወቅ ነው። የታቀደው የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ እና የታቀደው የክፍያ ጊዜ ሰሌዳን የሚያካትተው ሪፖርቱ፣ ለቋሚ ፖሊሲ ኮሚቴ (SPC) የማህበረሰብ እና መከላከያ አገልግሎቶች (CPS) ላይ በረቡዕ፣ ማርች 10, 2021 ይቀርባል።

በመጋቢት 5ኛ የኮሚቴ ስብሰባ አጀንዳ፣ የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማ ሪፖርት እና ተያያዥ ሰነዶች ተደራሽ እንዲሆኑ በሚከተለው አገናኝ መስመር እንዲገኙ ይደረጋሉ፥ https://www.calgary.ca/ca/city-clerks/legislative-services/agenda-minutes.html

**ለቋሚ ፖሊሲ ኮሚቴ ማቅረብ**

ባሁኑ የCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት፣ የኮሚቴ እና የምክር ቤት ስብሰባዎች ውስጥ በርቀት የመሳተፍ አማራጮችን ለማህበረሰብ እያቀረብን እንገኛለን። በዚህ ስብሰባ ውስጥ ለመሳተፍ ከወደዱ፣ የሚከተሉትን ሊያደርጉ ይችላሉ፥

- በቀጥታ ስርጭት የኮሚቴ ስብሰባውን መከታተል http://video.isilive.ca/calgary/live.html.
- የህዝብ ማስገቢያ ቅጽ በመጠቀም የጽሁፍ ማስገቢያን መፈፀም።
- በኮሚቴ ስብሰባው ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ለመመዝገብ የከተማው ጸሀፊ ቢሮን በኢሜይል publicsubmissions@calgary.ca ላይ ማግኘት። እባክዎ ያስታውሱ፣ ህዝቡ በአጀንዳ ይዘቱ የህዝብ መስማት ክፍለ-ጊዜ ወቅት ለአምስት ደቂቃዎች ለኮሚቴው ሊያቀርብ ይችላል። ለመናገር ፍላጎት ካለዎት፣ እባክዎ አስተያየቶችዎን በሪፖርቱ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮች ላይ እና በውይይት ያሉ የሚመከሩ እርምጃዎች ላይ ይገድቡ።

**የባለድርሻ አካል የመልስ ሪፖርት፥ የሰማነው ነገር**

የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማን ለመደገፍ የተዘጋጀው የQ4 2020 ደረጃ 2 ባለድርሻ አካል የተሳትፎ ሂደት አሁን ተጠናቋል። የተሳትፎ ሂደቱ እና ከኢንዱስትሪ ባለድርሻ አካላት የተሰበሰበ ግብረ መልስ ማጠቃለያ ሀሳብ የባለድርሻ አካሉ *የሰማነው ነገር ሪፖርት* ውስጥ ተካቷል።

የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማን በማስመልከት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ Calgary.ca ይጎብኙ።

ይህ መፅሔት በአማርኛ፣ ሂንዲ፣ ፑንጃቢ እና ኡርዱ ቋንቋዎች ጭምር በ Calgary.ca ይገኛል።

የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማን በማስመልከት ማንኛውም ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ltsengagement@calgary.ca ያግኙ።

የሊቬሪ ትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ ግምገማ ውስጥ ስላደረጉት ተሳትፎዎ እና ስለሰጡት ግብዓት እናመሰግናለን።
ከሰላምታ ጋር፣

አብዱል ራፊህ
ዋና የሊቬሪ ተቆጣጣሪ
ካልጋሪ የማህበረሰብ ደረጃዎች